## አምስቱ  አዕማደ ምሥጢር

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እምነቷን የምትገልጽበት ለሰዎችም የምታስተምርበትና የምትመሰክርበት አምስት አዕማደ ምሥጢራት አላት።

ሀ. አምስት ፦ ቁጥራቸውን ይገልፃል

ለ. አዕማድ፦ ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። አንድ ቤት ሲሰራ
ሊቆምና ጠንካራ ሊሆን የሚችለው በአዕማድ(ምሰሶዎች)ነውና።
ሃይማኖታችንም መሠረታዊ ምሰሶዎች አሏት።

ሐ. ምሥጢር፦ ለወዳጅ የሚገለጽ ነገር ሲሆን። ለሚያምኑ ሁሉ የሚገለጽና በእምነት ብቻ በመታየቱ ምሥጢር ይባላል።

አምስቱ  አዕማደ ምሥጢር የሚባሉትም፦

1. ምስጢረ ሥላሴ
2. ምስጢረ ሥጋዌ
3. ምስጢረ ጥምቀት
4. ምስጢረ ቁርባን
5. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው።

አንድ ክርስቲያን እነዚህን ጠንቅቆ ከተረዳ መሠረቱ ጠንካራው ነው አለት ይሆናል። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 14፥ 19 ላይ "አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ" ብሎ የአምስቱን አዕማደ ምሥጢር በእውቀት ለምዕመናን ያስተምር የነበረው።

### 1. ምስጢረ ሥላሴ

ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር 1ኛው ይህ ምስጢረ ሥላሴ ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር የአምላካችን አንድነትና ሦስትነት የሚገለጽበት ነው።

ሀ. አንድነት ፦ በመለኮት፣ በባሕርይ፣ በህልውና፣ በፈቃድ፣ በእዘዝ በአገዛዝ፣ ይህን አለም በመፍጠርና በማሳለፍ ይህን በመሳሰለው ሁሉ።

ለ. ሦስትነት፦ በስም፣ በግብር፣ በአካል

-በስም፦ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ (ማቴ. 28፥ 19)

-በግብር፦ አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ ነው። (ዮሐ. 14፥25)

-በአካል፦ ለአብ ፍጹም አካል፣ ለወልድ ፍጹም አካል ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል አለው (ማቴ. 3፥16)

ስለዚህ ሥላሴ በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ናቸው ብንልም በመለኮት፣ በህልውና፣ በባሕርይ፣ በእዘዝ በአገዛዝ በመሳሰሉት አንድ ስለሆኑ አንደ አምላክ ተብሎ ይታመናል ይጠራል እንጂ ሦስት አማልክት አይባልም። ከዚህም የተነሣ ሥላሴ ሦስት ሲሆኑ አንድ ሲሆኑ ሦስት በመሆናቸው ይህ ምሥጢር ተባለ ለሚያምን ብቻ የሚገለጽ ምስጢር።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

- አንድነት ፦ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" ዘፍ. 1፥1
- ሦስትነት ፦ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።" 2ቆሮ. 13፥14
- አንድነትና ሦስትነት፦ እግዚአብሔር አለ፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ዘፍ. 1፥26

ሌሎች ምሣሌዎች

1. ፀሐይ ፦ ሀ. ክበብ (ቅርፅ) አላት

ለ. ብርሃን አላት

ሐ. ሙቀት አላት

አንድ የሆነችው ፀሐይ - ክበብ፣ ብርሃን ፣ ሙቀት ስላላት ሦስት ፀሐይ አትባልም አንድ ፀሐይ እንጂ። በክበቡ አብ ይመሰላል በብርሃኑ ወልድ ይመሰላል በሙቀቱ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። አብ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ቢባሉም እርሱ ግን አንድ ፈጣሪ አምላክ ነው።

2. ነፍስ ፦ ሦስትነት አላት።

ሀ.ልብ

ለ.ቃል

ሐ.እንትንፋስ

ይህ ማለት ለባዊ ናት(ልብ)፣ ነባቢት ናት (ቃል) ሕያዊት ናት (እስትንፋስ) አሁን እንደምታዩት ልብ የምታደርግ፣ የምትናገር፣ ሕያው የሆነች ብለን ብንመለከትም ሦስት ነፍሳት ሳይሆን አንድ ነፍስ ብቻ ነች።

በአብ ልብ ይመሰላል፣ በቃል ወልድ ይመሰላል፣ በእስትንፋስ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ልክ እንደነፍስ ሦስትነት ሲኖራት አንድ እንዳልን ሥላሴም ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸውና አንድ አምላክ ብለን እናምናለን።

አስረጅ ንባባት

በብሉይ ኪዳን ፦ ዘፍ.1፥26 ዘፍ.2፥18 ዘፍ.3፥22 ዘፍ.11፥7 ዘፍ.18፥1 መዝ.32 (33) ፥5 ኢሳ.6፥3 ኢሳ.48፥12

በአዲስ ኪዳን፦ማቴ.3፥16 ማቴ.28፥19 ዮሐ.14፥26 2ቆሮ.14፥13 1ጴጥ1፥2 1ዮሐ.5፥7

ከብዙ በጥቂቱ ይህን ያህል ከገለጽን ሌላውን የቤተክርስርቲያናችንን የጠራ ወንጌል በመስማት እውቀታችሁን ይዛችሁ በእምነት ለመጽናት ትጉ። አንድ ሲሆን ሦስት ፣ ሦስት ሲሆኑ አንድ መሆኑ ምሥጢር ተባለ። የምሥጢር ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለሁላችንም ይግለጽልን።

## 2. ምሥጢረ ሥጋዌ

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ያለአባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው ሆኖ ከወደቅንበት የኀጢአት ጉድጓድ አወጣን አዳነን ብለን ሰው መሆኑን የምንረዳበት እምነት ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል።

### ከማን ሰው ሆነ?

በነቢዩ ኢሳይያስ 7፥14 "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ብሎ እንደተነገረ ሰው የሆነው ከድንግል ነው። በሉቃስ 1፥27 "የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።"

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ የወደቀውን አዳም ለማዳን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ተዋህዶ ሰው ሆነ። ይህ ሰው የሆነው አምላክ ነው። የሥጋን ባሕርይ ባሕርይው ያደረገ የማይታየው የታየው የማይዳሰሰው የተዳሰሰው ከእመቤታችን በተዋሃደው ሥጋ ነው ብሎ ማመን ምሥጢረ ሥጋዌን መረዳት ነው። መሠረታዊ ቃሉም በዮሐ. 1፥1-14 ያለው ነው። በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ነበር ብሎ "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን የእግዚአብሔር ከእመቤታችን መወለድ ይገልፃል።

## ሰው የሆነው ማነው?

እግዚአብሔር፦ ዮሐ. 1፥1-14
አምላክ ፦ ኢሳ. 9፥6
ጌታ መድኃኒት፦ ሉቃስ 2፥8-14

## ለምን ሰው ሆነ?

አዳም በበደለው በደል የሰው ልጅ ሁሉ ሞት ተፈርዶበት ከአምላኩ ተለይቶ ገነት መንግሥተ ሰማያትን አጥቶ በኃጢአት ወድቆ ስለነበር ይህ የወደቀውን አዳም ለማንሳት የሰው ልጅ ሁሉ ህይወትን ያገኝ ዘንድ የዲያብሎስ ባርያ የነበረው ደካማው የሰው ልጅ ብርቱ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን ያገኝ ዘንድ።ወልድን ፍቅር ከሰማይ ስቦት የመንግሥቱ ልጆች እንሆን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን
እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐ. 3፥16

"የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ" ገላ. 4፥4
ስለዚህ የዘላለም ህይወት እናገኝ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሀጢአት በስተቀር የሰውን ባህርይ ባህርዩ አድርጎ ፣ ያለመለወጥ፣ ያለመቀላቀል፣ ያለመለያየት፣ ያለመከፋፈል በተዋህዶ ሰው ሆነ።

ስለዚህም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእመቤታችን ተወልዶ የሰው ልጅን ሁሉ አዳነ። ስለዚህም አምላክ ሰው ሆነ ሰውም አምላክ ሆነ የሚለውን ምሥጢር በእምነት የተረዳ በጠንካራው አለት የተመሠረተ ነው።
"በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" ገላ 5፥1

ወልድ ሰው በመሆኑ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያነሰ ወይም የበለጠ አይደለም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ዘላለም ትክክል ነው። ብዙዎች የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆን ብቻ ያዩና ሀይሉን ማለት አምላክነቱን ይክዱታል (2ጢሞ. 3፥5) እርሱ ግን ዳኛ፣ ፈራጅ፣ ዘላለማዊ አምላክ ነው። በቸርነቱ ከሁላችን ጋር ይሁን።
"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው።ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ." ዕብ. 13፥8

## 3. ምስጢረ ጥምቀት

ከምስጢረ ሥላሴና ሥጋዌ ቀጥሎ ያለው ለሚያምኑም የሚሰጥ ለኃጢአት መደምሰሻ፣ ለዲያብሎስ ድል መንሻ፣ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ የሚያበቃ ከመንፈስ ቅዱስ የመወለድን ፀጋ ልጅነትን የሚያሰጥ ምስጢረ ጥምቀት ነው።

ልጅነትን የምታሰጥ ይህችን ጥምቀት የመሠረተልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

"ወአሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ኀበ ዮርዳኖስ ከመ የጠመቅ እምዮሐንስ" ያን ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ማቴ. 3፥13

በዚያን ጊዜም ዕድሜው የ30 ዘመን ጎልማሳ ነበር። በ30 ዘመኑ መጠመቁ አባታችን አዳምን ሲፈጥረው የ30 ዘመን ጎልማሳ አድርጎ ነበር።አዳምም የ30 ዘመን ሆኖ ተፈጥሮ የተሰጠውን ልጅነት በዲያቢሎስ አስነጥቆ ነበርና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ልጅነት ሊመልስለት በ30 ዘመኑ በዕደ ዮሐንስ በአፍላገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ።

**በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁም፦**

ሀ. ትንቢቱ ይፈፀም ዘንድ ነው። አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖስ ወደኋላሽ የተመለስሽ ምን ሆናችኋል" መዝ. 113(114) ፥5

ለ. ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ላይ የዕዳ ደብዳቤ ጽፎ በዮርዳኖስ ቀብሮት ስለነበር ያንን ለመደምሰስ

ሐ. በብሉይ በዮርዳኖስ ወንዝ (ጸበል) እየተጠመቁ ከስጋ ደዌ ይፈወሱ እንደነበር የነፍሳችንን ደዌ ሊፈውስልን በዮርዳኖስ ተጠመቀ። ለምሳሌ - ኢዮብ፣ ንዕማን (2ነገ. 5፥14)

በውኃ መጠመቁ

ሀ. ትንቢት ስላለ - "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ" ሕዝ . 36፥25

ለ. በማር ወይም በቅቤ አላደረገውም በውኃ ተጠመቀ ለድሃው ለሃብታሙ ለታላቅ ለታናሹ ለሁሉ ይገኛልና

ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ ለመዳን "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" ሊጠመቅ ይገባዋል። (ማቴ. 28፥19)

አንድ ሰው አምኖ በሚጠመቅበት ጊዜ ካህናት በጸሎት ውኃውን ሲባርኩት ልክ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ማየ ገቦ ይሆናል። (ዮሐ. 19፥34) በዚያን ጊዜም ከውኃና ከመንፈስ ይወለዳል። ይህችም ሁለተኛ ልደት ትባላለች። አንደኛ ልደት ከእናት ከአባት አለና - ጌታም የነገረን ይህንን ነው። "እውነትእውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ። "ዮሐ.3፥1-15

**ለመጠመቅ ዕድሜ**፦ ምን ያህል መሆን አለበት ለሚለው -

ሀ. ከእውነተኛይቱ እምነት ከተዋህዶ ውጪ ለሆነ ሰው። መጀመሪያ የቤተክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት መማር አለበት። ማመንም አለበት። ባመነም ጊዜም የሚሰጠውን ቀኖና ፈጽሞ ይጠመቃል።

ለ. ለክርስቲያን ለተዋህዶ አማኝ ለክርስቶስ ወገን ግን ቤተክርስቲያናችን ሥርዓትን ሰርታለች ይኸውም ወንዶች በተወለዱ በ40 ቀናቸው ሴቶች ደግሞ በ80 ቀናቸው ይጠመቁ ዘንድ። ይህም ምሳሌ አለው፦
1.አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋን ደግሞ በ80 ቀኗ ወደ ገነት መግባታቸው። (ኩፋሌ 4፥9)
2.ሴት ልጅ ወንድ ስትወልድና ሴት ስተወልድ የመንጻት ልማዱ ወንድ ከወለደች 40 ሴት ከወለደች 80 ቀን ስለነበር። (ዘሌ. 12)

በነዚህ ምሳሌዎች ቤተክርስቲያናችን ለክርስቲያን ልጆች እንዲህ ሥርዓትን ሰራች።

**ምሥጢር መባሉ** ፦ ሀ. በጸሎት ውኃው ተለውጦ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ውኃ ሲሆን በሥጋ ዓይን ስለማይታይ

ለ. ከመንፈስ ቅዱስ በምንወለድበት ጊዜ ልክ ከእናታችን ከአባታችን ስንወለድ እንደማናውቅ በዚያን ሰዓት ስለማንረዳ በመንፈስ የሚታወቅ በመሆኑ

## 4.ምሥጢረ ቁርባን

ይህ አራተኛው ምሥጢር ሲሆን እምነታችን የሚረጋገጥበት ለመንግሥተ ሰማያት ብቁ የሚያደርግ ማህተም ነው። የዘላለም ህይወት ለማግኘት የሰው ልጅ ሁሉ ምሥጢረ ቁርባንን ሊያምንና ሊፈጽም ይገባዋል።

ቊርባን ማለት፦ የጌታችንን የመድሐኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን አምኖ መቀበል ማለት ነው።

"ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና፦ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው። እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" ማቴ. 26፥26-28

## በመቁረብ ምን እናገኛለን

እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ያለሕግ አልተዋቸውም። የሰጣቸውም ሕግ ክፉንና ደጉን ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ነበር። በምክረ ሰይጣን ተታለው በበሉ ጊዜ ግን ወደቁ።አምላክም የሰውን ልጅ አልተወውምና ሊያድነው ከእመቤታችን ተወለደ። በቀራኒዮ በመስቀል ተሰቅሎም ደሙን አፍስሶ የሞተውን አዳምን ሕይወት ሰጠው። (ዘፍ. 3፥1 ገላ.4፥4 ማቴ. 27፥32-34)

ስለዚህ ሕይወትን ያገኘነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ነውና። ይህ በቀራኒዮ የተሰቀለልንን ቅዱስ ሥጋ ስንበላ ክቡር ደሙን ስንጠጣ የዘላለም ሕይወት ይኖረናል።ማለትም ጌታችን ከእኛ ጋራ እኛም ከጌታችን ጋራ ለዘላለም እንኖራለን።

> "የወልደ እጓለእመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም... ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ዮሐ. 6፥53-59

## ሥጋና ደሙ የሚሰጠው ለማን ነው

ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወቱን የሰጠው ለሁሉ ነውና ። በንስሀ ሕይወት በምክረ ካህን ያለ ክርስቲያን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ያገኝ ዘንድ ያለዕድሜ ገደብ ሥጋና ደሙን ይቀበል ዘንድ ይገባዋል። ቁርባን የሚከለክለው ዝሙት፣ ስርቆት፣ መግደል፣ ሐሜትና የመሳሰሉትን ሲሆን ከእነዚህ ርቆ በቅድስና ህይወት በመሆን ክርስቲያን ሁሉ ሥጋወደሙን ተቀብሎ ሊኖር ይገባዋል።

## ምሥጢር ለምን ተባለ

ኅብስቱ ተለውጠ ሥጋ መለኮት (የጌታ ሥጋ) ወይኑ ተቀይሮ ደመ መለኮት (የጌታን ደም) ሲሆን በሥጋ ዓይን ስለማይታይ ምስጢር ተባለ። እንድም በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋን ይሰጣልና ምሥጢር ተባለ።

## በምሥጢረ ቁርባን ምን እናስባለን

ሁል ጊዜ ቤተክርስቲያናችን ይህን የቁርባን ምሥጢር የምትፈጽመው በሥርዓተ ቅዳሴ ነው። ከቅዳሴ ውጪ ቁርባን የለም። ይህን የምናደርገው የጌታችን ሞቱን ለማሰብ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህን ባለመረዳት የጌታ ሥጋና ደም መታሰቢያ ይመስላቸዋል ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። መታሰቢያነቱ ለሞቱ ነውና።

> "እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው .... ስለ ብዙዎች ለኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ማቴ. 26፥26
>
> "…. ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ <u>ሞቱን</u> ትናገራላችሁና" 1 ቆሮ.11፥23-26
>
> ስለዚህ ለመታሰቢያዬ አድርጉት ሲል ለሞቱ መታሰቢያ ነው እንጂ ለሥጋን ለደሙ መታሰቢያ አይደለም። እራሱ ሥጋውና ደሙ ነውና

ቅዱስ ሥጋውን በልተን ክቡር ደሙን ጠጥተን የዘላለምን ሕይወት የወርሰን ዘንድ የመሐሪ አባታችን ቅዱስ ፈቃድ ለሁላችንም ይደረግ።

## 5.ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን አምስተኛው ምሥጢር ሲሆን ትርጉሙም የሰው ዘር ሁሉ ከመቃብር የሚወጣበት፡ ጻድቃን ለዘላለም ሕይወት፡ ኀጥአን ግን ለዘለለም ሞት ከመቃብር ሥጋቸው የሚነሳበት ማለት ነው። ነፍስ ደግሞ ከገነት ወይም ከሲኦል ወደ የማይበሰብስ ተመልሳ የምትወሰድበት።

አንድ ሰው ሞተ ስንል ነፍስና ሥጋ ሲለያዩ ነው። ሥጋ ወደ መቃብር ይወርዳል ነፍስ ደግሞ እንደሰውየው ሃይማኖትና ምግባር ወደገነት ወይም ወደ ሲኦል ይገባል። በትንሣኤ ጊዜ ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት አልያም ወደ ገሃነመ እሳት ይገባል።

<u>ገነት</u>፦ እስከ ትንሣኤ የጻድቃን ነፍስ የሚቀይባት ሥፍራ ናት።

<u>ሲኦል</u>፦ እስከ ትንሣኤ የኀጥአን ነፍስ የሚቀጣባት ሥፍራ ናት።

<u>መንግሥተ ሰማያት</u>፦ በትንሣኤ ጊዜ ለቅዱሳን የምትሰጥ የዘላለም ቤት።

<u>ገሃነም እሳት</u> ፦ በትንሣኤ ጊዜ የኀጥአን የመጨረሻ ፍርድና የሞት ቦታ ነች።

ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ አለም መጥቶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን ያፈሰሰው እኛ የዘላለምን ሕይወት እንድንወርስ ነው። ያ ደግሞ የሚሆነው በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ነው። በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም።

"...ኢየሱስም፦ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" ዮሐ. 11፥25

ጌታችን ይህንን እናምን ዘንድ በትምህርቱ ብቻ ሳይሆን በተአምራት አሳይቶናል።

ሀ. አልዓዛርን - ዮሐ. 11፥43

ለ. ወለተ ኢያኢሮስን - ማቴ 9፥25

ሐ. አንድ ጎበዝን ሌሎችንም ከሞት አንስቶ ሕይወት ሰጥቷል ሉቃ. 7፥15

መጽሓፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ስለ ትንሣኤ ሙታን ያስተምረናል፦

ኢሳ. 26፥19 ኢዮ.19፥25 ዳን.1 2፥1

ማቴ.22፥23-33 ማቴ.25፥31 ዮሐ.14፥1 1ኛቆሮ.15 2ኛ ጢሞ.4፥6-8

ምሥጢር የተባለበት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንደተነሣ ሁሉ ለእኛ ትንሣኤ በኩር እንደሆነልንና ብታምኑኝ እናንተም ትነሣላችሁ ብሎ እንዳስተማረን ሥጋችን ከሞተ ከበሰበሰ በኋላ መነሣታችንን ምሥጢር አስብሎታል። ይህ የሚበሰብሰው ሥጋችን ባለመበስበስ፣ የሚደክመው ባለመድከም የሚራበው ባለመራብ፣ የሚሞተው ባለመሞት በድካም የሚወድቀው በኀይል የሚነሣበት ነውና ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ተባለ።

"በዚያም ዘመን ስለሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል። በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ

ብዙዎቹ ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እረፍትና ወደዘላለም ጉስቁልና”
ዳን. 12፥1

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እልፍ አእላፋት ከሆኑ መላእክቱ ጋር ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በቀኙ ከሚቆሙት ቅዱሳን ጋር ያቆመን ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ይሁንልን።